# የእስልምና እምነት መቼና እንዴት ወደኢትዮጵያ ገባ

ወንድወሰን ሰብስቤ
England, coventery, 2009/22.2

አገራችን ኢትዮጵያ ከማንኛውም አፍሪካ ህገር ለአረባዊ ህገር የቀረበች  በመሆኑዋ የእስልምና እምነት ሊስፋፋ ችሉዋል:: ኢትዮጵያም  ለእልምና እምነት  ህልውና የዋለችው ውለታ እንዲህ ነበር::  ነብዮ መህመድ ለተከታዮቻቸው በሰጡት መመሪያ ኢትዮጵያን  በሚመለከት ህዝቡ በፍላጎቱ ከሰለመ ይስለም:: ከዚህ በተረፈ ግን እስልምናን ለማስፋፋት ሲባል በአንድም አበሻ ላይ አንድም ጉዳት  እንዳይደርስ:: አደራችሁን አበሾችን አትንኩ:: ህዝቡም ካልፈለገ በስተቀር በግድ ስለም አትበሉት ለምን አሉ?

የእስልምና እምነት ህልውና ከማግኘቱ በፊት ኢትዮጵያና አረቢያ የቆየ ትውቅ ነበራቸው:: ከብዙ ሺ አመታት ጀምሮ  ኢትዮጵያ የቆዳ ስፋቷ  እስከ የመን ስለሚደርስ ከአረቢያ የሚነሱ ጎሳዋች ወደሰሜን ኢትዮጵያ እየመጡ ይኖሩ ነበር:: ሲያስኛቸውም ወደህገራቸው  ይመለሳሉ:: በዚህ መልኩ አብሮ መኖርና ግንኙነት የጀመሩት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር:: ነቢዮ መህመድ የእስልምናን እምነት መስበክ ሲጀምሩ የአረቢያ ህዝብ የክርስትናን ገዢነት በተቃወሙበትና በተጋፈጡበት መልኩ በቆራይሾች የሚመራው ተቀዋሚ ነቢዮ መህመድን መቃወም ጀመረ:: ጉዳዮ በመቃወም ብቻ አልቆመም:: የእስልምና እምነት ሰባኪዋችና ተከታዮች በየሜዳው ይታረዱ ጀመር:: የእስልምና እምነት አስተማሪዎች እና ተከታዮች በአረቢያ ምድር መጨፍጨፍና ማለቅ ነቢዮ መህመድን አስጨነቃቸው:: የተከታዮቻቸው ህይውት መትረፍ አስፈላጊነቱ የወደፊቱን ሁኔታ የሚወስን  ሆኖ አገኙት:: እናም የክርስትና እምነት ተከታይ የሆነችውን ኢትዮጵያን መሸሸጊያና መጠጊያ ትሆን ዘንድ አሰቡዋት:: ኡርዋህ አልዙባይር ለአብደላ አብን ሜርዋን በላከው ደብዳቤ በዚያ የእስልምና እምነት ተከታዮች በየሜዳው እንደእንሥሳ እየታደኑ በሚገደሉበት ወቅት የቅርብ ተከታዮቻቸውን ወዳበሻ ሃገር ሂዱ፣ በአበሻ ንጉሥ ግዛት ውስት ማንም ሰው ከህግ ውጭ አይደለም፣ በደልም አይፈፅምበትም፣ በዚህ ህገር የደረሰባችሁ ስቃይና መከራ በአበሻ ህገር የለም::  ከዚያ እፎይ ብላችሁ ያለምንም ስጋትና ጭንቀት ስቃይና መከራ በሰላም ያኖሩዋችሁአል በማለት የኢትዮጵያውያንን መልካምነት ገልፅው ወደኢትዮጵያ አሰናበቱዋቸው::

የራሳቸው የነብዮ መሐመድ ልጅ የሆነችውን ፎቅያንና ባለቤቱዋ ኡስማንን ጨምሮ 12 ወንዶችና 5 ሴቶች በአጠቃላይ 17 የእምነቱ ተከታዮች ወደኢትዮጵያ ተሰደዱ:: ይህንኑ ስደት አስመልክተው ኤስ ፋጡማ የተባሉ ፅሀፊ በአንድ የፓኪስታን ጀርናል ላይ  በ 1961 ላይ ባቀረቡት ፅሁፍ በእስልምና እምነት መሰረት ሄጅራ የህይማኖት ስደት አህዱ የተባለው በነዚህ 17 ሙስሊሞች በ 615 ላይ የእስልምና እምነት ከበቀለበት ከመካ ከተማ መጀመሪያ ክርስትና እምነት ወደተቀበለችው ወደ ኢትዮጵያ ያደረጉት ስደት ነው ይላሉ::

በዘመኑ የአስልምና ህይማኖት ተከታዮችን እያሳደዱ ይጨርሱ የነበሩትን የቆራይሽ ጎሳዎች ነቢዩ መህመድ ወደኢትዮጵያ የላኩዋቸው አማኞች አሳደው የመያዝ ጦር ቢያንቀሳቅሱም ሊደርሱባቸው አልቻሉም:: ስደተኞቹም ኢትዮጵያ ምድር እንደደረሱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ንጉስ አርማህ እና ህዝቡ ወንድማዊ አቀባበል አደረጉላቸው:: የነዚህ ስደተኞች በኢትዮጵያ በሰላምና በደስታ መኖር ለነቢዮና ለእስልምና ተከታዮች በአጠቃላይ ትልቅ ተስፋ ሆናቸው:: በዚህ በጭንቀት ሰአት የኢትዮጵያ ህዝብ አቀባበል የማረካቸው ነቢዮ ተጨማሪ የእምነቱን ተከታዮች ዳግም ወደኢትዮጵያ ጉዞ አደረጉ:: በዚሁ መሰረት 89 ወንዶችና 18 ሴቶች ጠቅላላ 107 ዳግም ወደኢትዮጵያ ጀአፋር አቡጣሊብ በተባለ የነቢዮ አጎት ልጅ እየተመራ አክሱም ከተማ ገባ::ይኸኛውም ቡድን እንደመጀመሪያው በሰላም መኖር ጀመረ:: ይሁን እንጂ የእስልምና ተከታዮች በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም መኖር ቁራይሾችን አስከፋቸው:: እሰላሞች በኢትዮጵያ በስላም መኖር ለነሱ

እንደትልቅ አደጋ ሆነባቸው:: ስለዚህ ከኢትዮጵያ ንጉስ ጋር ምክር ማድረጉን ምርጫቸው አድርገው በንግግር አዋቂነታቸዉና በማሳመን ችሎታቸው የታወቁትንና የታመነባቸውን አብዱላ አቡራኪና አምር ወይሶ የተባሉ ተከታዮች ወደ አክሱም ተላኩ:: የመልክተኞቹ ተልእኮ ዋነኛ አላማ የሙስሊም ስደተኞች የክርስትና እምነት ጠላቶች መሆናቸውን በውሸት ለኢትዮጵያ ንጉስ ነግረውና አሳምነው ወዲያውኑ ከኢትዮጵያ እንዲባረሩ፤ አለዚያም በዚያው እርምጃ እንዲወሰድባቸው፤ ስደተኞቹ ወደ አረቢያ ተይዘውም ከተመለሱ በክህደት ተወንጅለው በአደባባይ በሰይፍ ሊያሰቅሏችውና ለወደፊቱም ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆኑ ለማድረግ ነበር:: ሁለቱም ተወካዮች ብዛት ያለው ውድ የሆነ ስጦታ እቃ ይዘው አክሱም ደረሱ:: በቅድሚያ ወደ ንጉሱ ዘንድ ቀርበው ስደተኞቹ ያገራቸውን እምነት የካዱና የክርስትናን እምነት እያንኳሰሱ አዲስና ለማንም የማይበጅ እምነት እያራመዱ መሆናቸውን ተናገሩ:: ይልቁንም ህዝቡንና ሀይማኖቱን ሳይበክሉ ባፋጣኝ እንዲያባርሩአቸው በሰላሙ አንደበታቸው ኑጉሱን ለማሳመን ጣሩ:: ንጉስ አርማህም የመልአክተኞቹን ወሬ ሰምተው እርምጃ ለመውሰድ አልቸኮሉም:: ይልቁንም ስደተኞቹን በማስጠራትና ነባር እምነታቸውን የተውበትን ምክንያት ከባለጉዳዮቹ አንደበት መስማት መረጡ:: ከዚያም ተወካይ ጃአፈር አቡጣሊብ ተገቢ ምላሽ መስጠት ብቻ ሳይሆን መልክተኞቹም ማርያምንና ልጇዋን ክርስቶስን የሚኮንኑ ቁጥር አንድ የክርስትና እምነት ጠላቶች ናቸው በማለት በአደባባይ በንጉሱ ፊት ወነጀላቸው::

ፕሮፌሰር ስርገው ሀይለስላሴ የጥንታዊው የመካከለኛውና የኢትዮጵያ ታሪክ በ1270 ዓ/ም በሚለው መፅሀፋቸው ተርሚኒግ ሀምንና ሽሮዳርን ጠቅሰው እንዳሰፈሩት ጃፋር ክርስቶስ የፈጣሪ መልክተኛ በመሆን በመንፈስ ተፀንሶ ከማሪያም በሰው አምሳል መወለዱን በእስልምና እንደሚታመንበት ለንጉሱ ማስረዳቱንና ንጉሱም በምላሹ እረክተው ስለ ማሪያም ምን ትላላችሁ ብለው መጠየቃቸውንና ጃፋርም በቅዱስ ቁራአን በምዕራፍ 19 ከቁጥር 16-34 የሰፈረውን አንብቦላቸው፤ ይህም በመፅሀፍ ቅዱስ በሉቃስ ምራፍ 1 ከቁጥር 47-55 ስለማርያም ከሰፈረው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን መግለጹን ለመረጃ አኑረውልናል:: በስርገው ሀብተስላሴ መስረት ንጉሡ በመልሱ መመሰጥ ብቻ ሳይሆን ሪዛቸው በእንባ እስከሚርስ ድረስ አልቅሰዋል:: አብረዋቸው የነበሩትም የቤተክርስቲያኑዋ  አገልጋዮች የያዙት መፅሀፍ እስከሚርስ ድረስ አንብተዋል ንጉሥ አርማህ በተሰጠው መልስና በነሱ አቀራረብ ተደነቁ:: ለርምጃም ሳይቸኩሉ አውጥተውና አውርደው: እንዲህ ሲሉ ተናገሩ - ሁላችንም እንደሰማነው ከሆነ እነዚህ የአምላክ ፍጥረቶች የክርስትና እምነትን የሚያንቋሽሹ አንድም ቃል አልወጣቸውም:: አንድም አዲሱ እምነታቸው ትክክል ከክርስትና እምነታችን ጋር ተመሳሳይ ተቀራራቢ ስለሆነ: የነዚህ ሰዎች ጠላትነት ስላልታየኝ: እናንተ ተራራ የሚያክል የወርቅ ቁልል እንኩዋን ብታመጡልኝ እኔና ሀገሬን ህዝቤን አምነው የተጠጉትን የእግዚአብሄር እንግዶች ምንም በሀይማኖት ባይመስሉኝም አሳልፌ ለናንተ አልሰጣችሁም:: ይልቁንም የናንተ ጉዳይ እዚህ ላይ የሚያበቃ ስለመሰለኝ ባፋጣኝ ሀገሬን ለቃችሁ ውጡልኝ በማለት የመለሱላቸው ሲሆን: በንጉሡም ውሳኔ ቀራይሾች ደንግጠው ባህር ተሻግረው የዘረጉት የተንኮል ውጥመድ ተበጣጠሰባቸው:: ነቢዮ መሀመድም በአበሻ ንጉሥ ግዛት ማንም ሰው ከህግ ውጭ  በደል እንደማይደርስበት አረጋገጡ:: በሃይማኖትም ተፀኖ ባለማድረጋቸው በኢትዮጵያና በእስልምና ተከታዮች ሀገራት መካከል መቀራረብን ፈጥሩዋል::

ቁራይሾችም ይህንን እንደሽንፈት አድርገው ቆጠሩት:: በዚህም የእስልምና ሀይማኖትን ለማጥፋትና ተከታዮችንም እንደበግ ማረድና መጨፍጨፍ ምርጫቸው አድርገው ተያያዙት:: እያፈሱም በእስር ቤት ማጎር; ኢኮኖሚውን ማህበራዊ ግኑኝነቱን በመገደብ ብቻ ሳይሆን እስልምና ከማይከተለው ጋር ጋብቻ እንዳይፈጽሙ በህግ ከለከሉ:: ጊልድዚሄር የተባሉ ጸሀፊ በ1967 የእስልምና ጥናት በተባለው መጽሐፋቸው ኢትዮጵያውያንና ንጉሳቸው ለነቢዮ መሐመድና ለተከታዮቻቸው የሰጡት ከለላና ያደረጉት እንክብካቤ በእስልምና እምነትና በእስላሞች ዘንድ ዝንት አለም ሲወደስና ሲሞገስ  የሚኖር ነው:: እስላሞች የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች ውለታ መርሳት የለባቸውም በለዋል:: በጊዜ እርዝመት ቀራይሾች በእስልምና እምነትና በተከታዮቻቸው ላይ የከፈቱት የጥቃት ዘመቻ እየተዳከመና እመነቱ በአንጻሩ መጠነኛ ተቀባይነት እያገኘ ሲመጣ ነቢዮ መሐመድ በኢትዮጵያ የሚገኙ ተከታዮቻቸው ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ለማድረግ መልክተኛ  ወደኢትዮጵያ ሰደዱ:: የራሳቸውን ፍቅርና አገሩን ጭምር ለእስልምና እምነት ተከታዮች

ያልነፈጉት ንጉስ አርማህም የነብዩን መልክትና መልክተኞች በአክብሮት ተቀብሎ ወደ ህገራቸው ሲመለሱም ለመጓጓዣ ይሆን ዘንድ ሁለት መርከቦችን አዘጋጁ:: ይሁን እንጂ እነዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩት ስደተኞች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ሲነገራቸው እሽታቸውን የገለጹት 16ቱ ብቻ ሲሆኑ 58/ እጅ ያህሉ ግን የኢትዮጲያ ንጉስና ህዝብ ባደረጉላቸው እንክብካቤ ልባዊ ፍቅር ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩን ምርጫቸው አደረጉ:: ነቢዩ መህመድ ከኢትዮጵያ ከንጉስ አርማህ ጋር በነበራቸው ግኙኙነት መሰረት የአቡሱፊያ ልጅ የሆነቸውን ኡምህቢባን እንዲድርላቸው ንጉሰ አርማህን ጠየቁት:: ኡሚህቢባ ያገባች ነበረች:: ነገር ግን አብሩዋት ወደ ኢትዮጵያ ተሰዶ የነበረው አቢድ አላህ አብደላ በምድር አረቢያ ይኖሩ የነበሩ እስልምና በፈቃዳቸው የተቀበሉ እንደነበር ሁሉ እሱም የክርስትናን እምነት በፈቃድ ተቀብሎ ተፋተው ነበር:: አርማህ ከነቢዩ መህመድ የቀረበላቸውን የጋበቻ ጥያቄ በደስታ ተቀበሉ::

አልማሱዲ የሚባሉት ፀሀፊ እንደፃፉት ንጉሱ ኡሚህቢባን እንደ ልጃቸው በመቁጠር 400 ዲናር /200/ ፓውንድ ጥሎሽ በመስጠት በክብር ዳሩዋትት:: ምርጥ በቅሎዎችንና ከነሙሉ እቃዎች አዘጋጅተው ሙሽሪት ኡምህቢባን ኳኩለው ለተመላሾችም በቂ ስንቅ ሰጥተው ሸኙዋቸው:: ስደተኞቹ በጃዓፋር መሪነት ወደ ህገራቸው የገቡበት ወቅትም እስላሞች ከበር በተባለ ስፍራ ትልቅ ድል የተቀዳጀበት ስፍራ ስለነበር ልዩ ትርጉም ተስጥቶት ነበር:: ነቢዩ መህመድ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያ ላይ ልዩ ፍቅር አደረባቸው:: የህዝቡንም ምንነት በሚገባ ተረዱ:: የህዝቡንም ታሪክና ባህል ከማወቅ አልፈው በንግግራቸው የግእዝን ቋንቋ መናገር ጀመሩ:: ለህዝቦቹም ባላቸው ፍቅርም በአጠገባቸው ከነበሩት ኢትዮጵያውያን መካከል “ቢላል” የሚባል ነብዩ ለትልቅ ሹመት አብቀተውታል:: መሾምንም ያጎናፀፈው ማራኪ ድምፁ ነበር:: ቢላል ምእመናንን ለፀሎት ሲጠራ ድምፁ ያምራል:: በዚህም ምክንያት የመካው ታላቁ መስጊድ አዛኒ /ምእመናንን ለጸሎት ጠሪ/ አደረጉት:: ሐልን ኢብራሂም ሐሰን የተባሉትም ፀህፊ በመካ ውስጥ ከቢላል በሆላ አዛኒት ለኢትዮጵያውያን እስላሞች ብቻ የሚሰጥ ሹመት እስከመሆን ደርሿል ብለዋል:: አህመድ ጀብር የተባሉት ሌላው ፀህፊ ደግሞ የነቢዩ የእጅ ቀለበትና /መህመድ የአላህ ነቢይ/ የሚል ጽሁፍ የተቀረፀበት ማህተም ሳይቀር የተሰራው ከኢትዮጲያ ከመጣ እንቁና የከበረ ድንጋይ መሆኑን ገልፀዋል:: ነቢዩ የህይወታቸው ፍፃሜም በደረሰ ጊዜ እንሆ በራሳቸው ልዩ ትእዛዝ ከኢትዮጵያ የተወሰደላቸውን ልዩ መድህኒት በአፋቸው እንደያዙ ለህልፈተ ህይወት መብቃታቸውን ጸህፊዎች ይጠቁማሉ:: የኢትዮጵያም ንጉስ አርማህ ሲሞቱም ነቢዩ መህመድ ልባቸው በህዘን ስለተነካ በመዲና ከተማም “ፊቱህ ኢል ህበሻ” የፍትሀት ፀሎት አስደረጉላቸው:: “አበሾችን ካልነኳችሁ አትንኳቸው” የሚለው የነቢዩ መህመድ የትላንት የሰላም ቃል ዛሬም በሙስሊም ሀገራት ሁሉ ሊታወስ የሚገባው ነው እንላለን::